አንባቢ ሆይ! ቁም!!! ወደ ሁሉ ነገር ተዘሎ አይገባምና፤
በመጀመሪያ “የምስክርነቱ” ዓላማ ለጌታ ክብር፣ ለሰው ጥቅም፣
ለሌባው ውርደትና የሰረቀውን 7 እጥፍ ለማስመለስ ስለሆነ
በዚህ መንፈስ ተነቃቅተው ያንብቡ እንጂ ለሥጋ ለባሽ
የማይገባውን ግምት በመስጠት ገለው እንዳይሞቱ ይጠንቀቁ!!!
መልካም ንባብ!!!

## *በክርስትና ላይ ጥናታዊ ምርምር ሲያደርግ የነበረው ሰው በራሱ ሕይወት ላይ ምርመራ ተደረጎበት እጁን ሰጠ!!!*

### *1) ቅድመ ክርስትና ሕይወት፡-*

ወንድ ልጅ ሲወለድ አባት ለተወለደው ልጁ ጠብ - መንጃ (ጠመንጃ) ለመግዛት ደፋ ቀና ከሚባልበት አካባቢ ነው ተወልጄ ያደኩት፡፡ ይህ የሚደረገው ደግሞ በቂ ሃብት ስላለ ሳይሆን “ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልሆነ እንደ አባቱ እንዝርት አቅርቡለት ይፍተል እንደ እናቱ” የሚለው የንቀት አባባል በልጁ ላይ ሲያድግ እንዳይደርስበት ከወዲሁ ለማዘጋጀት ነው፡፡ እንዲያውም ልጅ በልጅ ተሸንፎና ተመትቶ እያለቀሰ ወደ ወላጆቹ ለእርዳታ ሲቀርብ አልቃሻ ልጅ አልወድም/የለኝም ተብሎ በጥፊ ወይም በአለንጋ ይደገማል፡፡ በለው!፣ ትሸነፍና ወዮለህ!፣ እንዳታሳፍረኝ!፣ የሴት ልጅ!፣ (ከወንድ ብቻ የተወለደ ያለ ይመስል)፣ ሊጥ አትሁን!፣ አስለቅስ እንጂ አታልቅስ!፤ አትበለጥ!፤ ኩራት እራቱ!፤ ከአረባባ ግልድም ሙልጭ ያለ ቂ..... ይሻላል!፤ ከማን አንሼ!፤ .... ወዘተ እየተባልንና እያልን ነው እኛ ኢትዮጵያውያን በአብዛኛው ያደግነው፡፡ለዚህ ሳይሆን አይቀርም ተመካክረን ለአገር/ለሕዝብ ጥቅም የሚሆን በጎ ሥራ በሁሉም መስክ መሥራትና ከእኛ የተሻለውን ወንድማችንን ሳይቀር መሪ አድርገን መቀበል ያቃተን፡፡ “ማን ከማን ያንሳል” በሚል ትቢትና ንቀት ምክንያት መሆኑ ነው፡፡ የፈለገውን ያህል ይራቀቅና ይጠበብ እንጂ አበሻ በአበሻ እውቀት አይተማመንም፡፡ እስከ አሁን ድረስ መድሃኒት ያልተገኘለት በሺታችን ይህ የራሳችንን ሰው ችሎታ አምነን በመቀበል መጠቀም አለመቻላችን ነው፡፡ ተግባራዊ ሲደረግ አይታይም እንጂ በተለይ ክርስቲያን “ለወገኔ ይጠቅማል በማለት ወይም በከንቱ ውዳሴ ምክንያት አንድ እንኳ አታድርጉ፤ ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቁጠር፤ እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ” (ፊልጵ 2፡3-4) የሚል ዘላለማዊ የትዕዛዝ ቃል ተሰጥቶት ነበር፡፡

የእከሌ ልጅ ጎበዝ ነው ወይም ጀግና ነው ከተባለ ወላጆች ደስ ይላቸዋል፡፡ እኔም ይህን እያየሁ በማደጌ ከልጅነቴ ጀምሮ ከሰዎች በተለይ ከአባቴ በዚህ መንገድ ሙገሳ ማግኘትን እወድ ነበር፡፡ ይህን መሻቴን እውን/ተግባራዊ ለማድረግ ስል ደግሞ የማልሆነው ነገር አለነበረኝም፡፡ ከሁሉም በላይ ፈሪ ተብሎ መሰደብን እጠላ ስለነበር በእድሜም በአቅምም ከእኔ በላይ የሆኑትን የሰፈር ልጆች ሁሉ ዱላ ወይም ቡጢ እጋጠማቸው ነበር፡፡ ከዚህ የተነሳ መሰለኝ ከንግግሬ ይልቅ እጄን ለመሰንዘር ይቀናኝ የነበረው፡፡ አንባቢ ልብ ይበል! የነበረው አልኩ እንጂ አሁን ያለው አላልኩም ፤ **የእኔ የምለው እጅ በአሁኑ ወቅት ጨርሶ የለኝምና፡፡**

ትዝ ይለኛል ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ በነበርኩበት ወቅት አንድ ቀን ማታ ከአንድ ገራገር ጓደኛዬ ጋር በመሆን ሰርግ ወደነበረበት የጎረቤት ቤት ተያይዘን መሄዳችን፤ በዚያም ከማናውቃቸውና ጠብ ያለሽ በዳቦ ከሚሉ ጎረምሶች ጋር ፊት ለፊት ተፋጠጥን፡፡ ሁሉንም ሰው ሲያንጓጥጡ ለእኔና አብሮኝ ለነበረው ጓደኛዬም የግልምጫ ድርሻችን በንቀት ተወረወረልን፡፡ እነሱ በቁጥር ከእኛ እጥፍ በመሆናቸው ሊያጠቁን እንደሚችሉ ማመዛዘን አልቻልኩም፡፡ እጄ ላይም በትር አልነበረም፤ ቦክስ የሚባለውን ነገር ደግሞ የማውቀው በስም እንጂ በተግባር ሞክሬው አላውቅም፡፡ አተነፋፈሴ ፍጥነቱን ጨምሮ ፍርሃት አይሉት ድንጋጤ መላ ሰውነቴ ወባ እንደያዘው ሰው ተንቀጠቀጠ፡፡ እንደምንም ብዬ እራሴን በመቆጣጠር ዙሪያዬን ስቃኝ ከቤቱ ጥግ በተቀመጠ ፍልጥ ላይ ዐይኖቼ ድንገት አረፉ፡፡ እንዴት እንዳነሳሁትና አንደኛው ተሳዳቢ ሰውነት ላይ እንዳሳረፍኩት አላውቅም፡፡ ወዲያው መሬት ላይ ተዘረረ፤ ሌሎችም እግሬ አውጪኝ ብለው ተፈተለኩ፡፡ ከዚያም ትንፋሼ ወደነበረበት ስለተመለሰና የድል ስሜት ስለተሰማኝ የወደቀውን ልጅ በተንደባለለበት ላይ ሁለተኛ ልደግመው አልፈለኩም፡፡ “የፈሪ በትር” እንዳይባልብኝ ጭምር መጠንቀቄ መሆኑ ነው፡፡ እኔም ልጆቹን ከተመረራቸው የሰፈሩ ኗሪ ሕዝብ ሙገሳ ሲቸረኝ ግዳይ እንደጣለ ጀግና በኩራት ስሜት ዙሪያውን መጎማለሌ ትውስ ይለኛል፡፡ አይ ያ! የልጅነት ጊዜ! ሁሉ ነገር ለታይታና ለሙገሳ ተብሎ ካለማስተዋል በስሜት ብቻ በመነዳት የሚደረግበት ዘመን!!!

እኔና አብሮኝ የነበረው ቀሰስተኛ ጓደኛዬ ትንሽ ቆይተን ወደ ቤታችን ማምራት ጀመርን፡፡ አገር ጤና ብለን ድላችንን እያወራን በመጓዝ ላይ እያለን ዙሪያችን በበረካታ ጎረምሶች ተከቦ አገኘነው፡፡ ጨለማ ስለነበረ ደግሞ እንደ ልብ ማየት አልቻልንም፡፡ ሆኖም ግን ፍልጡን ይዤው ስለነበር ፊት ለፊት ያገኘኋቸውን አስበርግጌ መለስ ስል ያ! ቀደም ብሎ ፈጣኑን እጄን ቀምሶ የወደቀው ልጅ ከኋላዬ በቅርብ እርቀት ያዘውን ድንጋይ ፊቴ ላይ እንደ መብረቅ አንባርቆብኝ ተያይዘው እየፎከሩ ሸሹ ፡፡ ደገሞስ ማን አቅምና ወኔ አግኝቶ ሊከተላቸው? እኔም ወድቄያለሁ፤ አብሮኝ የነበረውም ሰው ቀደም ብዬ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ሊረዳኛና ሊያሳድዳቸው ይቅርና ጮኾ እርዳታ ሊጠራልኝ እንኳ አልሞከረም፡፡ እኔም ዘመድ ተጠርቶ በመምጣት ወደ ሆስፒታል እስከምወሰድ ድረስ

መብረቅ  እንደ ጣለው ዛፍ በፊንታዬ ምድር ላይ ተዘርግቼ ለሰዓታት መቆየቴ ይታወሰኛል፡፡ የዘሩትን መልሶ ማጨድ ማለት ይኸው አይደል? የሚገርመው ደግሞ ይህ ከዚህ በላይ የተገለጸው የትዕቢትና የመደባደብ ባሕሪዬ በተግባር የታየው በኢሕአፓ ምልምልነቴና መልማይነቴ ሁለት ጊዜ ታስሬ ከተፈታሁ በኋላ መሆኑ ነው፡፡ ቶርች መግባትና ታስሮ መፈታት ሊያሻሽለው ያልቻለን ባሕሪ ተሸክሜ በደረስኩበት ሁሉ ተግባራዊ ለማድረግ የምሻ ተቅበዝባዥ ጎረምሳ!!!

10ኛ ክፍልና ከዚያ በላይ የነበረው ተማሪ በሙሉ በ1967 ዓ/ም **ለእድገት በሕብረት ዘመቻ ሲዘምት** እኔ ግን ከ9ኛ ወደ 10ኛ ክፍል ያለፍኩበት ወቅት ስለነበረ ለጥቂት አመለጠኝ፡፡ ባለመዘመቴም እጅግ ተበሳጭቻለሁ፡፡ 11ኛ ክፍል በነበርኩበት በ1968 ዓ/ም በት/ቤቱ ዳይሬክተርና በክፍል ተቆጣጣሪ/ስም ጠሪ/ አስተማሪዬ ምክክር ለኢሕአፓ አባልነት ተመለመልኩ፡፡ ጉዳዩና ዓላማው ባይገባኝም በት/ቤቱ ውስጥ ከሚከበሩና አሉ ከሚባሉ ከእነዚህ ሰዎች ጥያቄው ስለቀረበለኝ ብቻ ጥሪውን በደስታ ተቀበልኩት፡፡ ወዲያውም በሴል ተይዤ ፍልስፍናውን ከሌሎች ጋር በመሆን ማጥናት ጀመርኩ፡፡

በዚህ ወቅት አንዳንድ ዘማቾች የተመደቡበትን ጣቢያ ለቀው በመምጣት **"ትምህርት ከድል በኋላ"** በማለት በት/ቤታችን ውስጥ በድብቅ ቅስቀሳውን አጧጡፈውት ስለነበር በተረጋጋ መንፈስ መማር አልቻልንም ነበር፡፡ እኔም ከሌሎች አባላት ጋር በመሆን የወቅቱን ፍልስፍና ጥናት ከድርጅቱ ዓላማ ጋር በማዛመድ በሕቡ ማጥናት እንደጀመርኩ የክፍለ ሃገሩ ግብርና ሚኒስቴር ዋና ጽ/ትቤ 6 የእንስሳት ጤና ጠባቂዎችን አወዳድሮና አሰልጥኖ ለመቅጠር ማሰታወቂያ አወጣ፡፡ አንዳንዱ ግርግሩን ለጊዜው ለማምለጥ ሲል፣ ሌላው ደግሞ ሥራ ለመያዝ ብሎ በርካታ ሰው ተመዘገበ፤ ቢሆንም ግን ከጠቅላላው ተመዝጋቢ ውስጥ 300 የምንሆን ለጽሑፍ ፈተና መቅረባችንን አስታውሳለሁ፡፡ ሥራው ከአርሶ አደሮች ጋር የሚያገናኝ ስለነበረ **ለወቅቱ የኢሕአፓ መዋቅር በየስፍራው የመዘርጋት ሥራ** ለመጠቀም ሲባል የድርጅቱ አባላት የነበርን በብዛት ተመካክረን ተመዘገብን፡፡ ከዚያም የተሰጠውን የእንግሊዝኛና የሒሳብ መመዘኛ ፈተና ካለፉት 6 ሰዎች መካከል የእኔ ስም በተራ ቁጥር ሁለት ላይ ወጣ፡፡ ት/ቤታችንም በመዘጋት ላይ ስለነበር በሁለቱ መልማዮቼ ምክር የሥራ ቅጥሩን እንድቀበል ተደረኩ፡፡ የሚኒስቴር መ/ቤቱም በወር ብር 95 እየከፈለኝ (በዚያን ጊዜ ብዙ ገንዘብ ነበር) ስልጠናውን በቻይና ሙያተኞች ለስድስት ወር በሌላ ስፍራ ለመውሰድ ተንቀሳቀስኩ፡፡ ይህ እንግዲህ ሚያዝያ ወር 1968 ዓ/ም መሆኑ ነው፡፡

ስልጠናውን በማጠናቀቅ ላይ እንዳለሁ የተጠናወተኝ የጠበኛነት በሽታዬ አብሮኝ ተጎዞ ስለነበር በስልጠናው ላይ እንዳለሁ **በበርዲዞ** (የወንድ እንስሳ ብልት ማንኮላሻ መሳሪያ) **የአንድ ነባር ሠራተኛ ጥርስ አፍልሼ** ወደ መጣሁበት ስፍራ ተመለስኩ፡፡ በዛሬ ማንነቴ ላይ አቅምና ስልጣን ባይኖረውም በዚያን ጊዜ **"ያደቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይለቅም"** (ካቀሰሰ በኋላ እንዴትና በምን ኃይል እንደሚለቅ ባላውቅም) ተብሎ ተ**ሚ**ርቶብኛል፡፡ **ሚ**ርትንና **ሚ**ርተኛነትን የሚሰብረው ሰባሪ በራሱ ጊዜ ቀድሞ በማስጣል ለዛሬው ማንነቴ አበቃኝ እንጂ!!!

እጅግ የሚገርመኝና እጄን በአፌ ላይ እንድጭን የሚያደርገኝ ጉዳይ ደግሞ በዚያን ወቅት ይህን ያሉኝ ሰዎች **"በትናንትናው እና በዛሬው እኔነቴ"** መካከል ያለውን ሰፊ ልዩነት ዛሬም ማየት አለመቻላቸው ነው፡፡ ታዲያ! እኔም የእነዚህን ጆሮ ዳባ ልበስ ያሉትን ዘመዶቼንና አብሮ አደግ ጓደኞቼን ሕይወት ቆም በማለት ሳስብ  ይህ **የምህረት አምላክ አንድ እጅግ ታላቅ የሆነ ተራራ ንዶና ደልዳላ ሜዳ አድርጎ በራሱ መለኮታዊ ስልጣን ወደ ራሱ እንዳቀረበኝ** ከልቤ በመረዳት ለዚህ ባለውለታና ታዳጊ የፍቅር ጌታ **"አቤቱ እኔ ማነኝ ቤቴስ ምንድነው ለዚህ ያበቃሃኝ"** በማለት ጉልበቴ ፈጥኖ መሬት ላይ ይነጠፍለታል፡፡ ከዚህ በላይ ልሆንለት የምችለው ነገር ስለሌለኝ እንጂ ይህም እጅግ ያንስበታል፡፡ የሚገርም የፍቅር አምላክ!!!

በዚያን ጊዜ ጥርስ በበርዲዞ ብሰብርም አልተከሰስኩም አለታሰርኩምም፡፡ እንዲያውም ወደ ተቀጠርኩበት ስፍራ የተመለስኩት ስልጠናው እየተጠናቀቀ በነበረበት ጊዜ ስለነበረ ሥራውን ለመጀመር ችግር አልገጠመኝም ነበር፡፡ ለምደባም ሁለት ክፍት የሆኑ አውራጃዎች በክፍለ ሀገሩ ጽ/ቤት በኩል ለምርጫ ቀርበውልኝ እንድመርጥ በክብር ተጠየቅሁ፡፡ እኔም ከሁለቱ የሥራ ቦታዎች መካከል ለዋናው የኢሕአፓ ሥራዬ ምቹ የሆነውን በትክክል ለመምረጥ እችል ዘንድ የበላይ አካል ማማከሬን አስታውሳለሁ፡፡ ከበላይ ተወስኖ ወደታች ለሚፈስ የውሳኔ ሃሳብ መገዛትንና ዓላማን በቆራጥነት ፈጽሞ ማስፈጸምን እንደሚገባ የተማርኩት ከዚች ድርጅት ነው፡፡ (ደርግስ አላመሰገነም እንጂ ከኢሕአፓ ብዙ ቁም ነገር ተምሮ አልነበረምን?) በመልማዮቼ በተመከርኩት ምክር መሰረት የበለጠ ተረጋግቼ የድርጅቱን ሥራ ወደምሠራበትና ችግር ቢፈጠር በቀላሉ መደበቂያ/መሸሸጊያ ወደማግኝበት አውራጃ ከሌሎች ጓዶች ጋር ለመገናኘት የሚያበቃኝን የሚስጢር ኮድ ተቀብዬ በመሄድ ተቀላቀልኩ፡፡

ጠላቱን ደምዝ እየከፈለ መውደቁን እንዲያፋጥንለት ሳያውቅ ሥራ የሚቀጥር መንግሥት መኖሩን ያረጋገጥኩት በዚያን ጊዜ ነበር፡፡ ለነገሩ እሱም ቢሆን(ደርግ) እንዲህ እንደምንለው ዋዛ ስላለነበረ የራሱን ሰዎች በዚች ድርጅት ውስጥ አስርጎ በማስገባት ዳግመኛ እንዳታገግምና እንዳታንሰራራ አድርጎ በፈረጠመ ጡንቻው አድቅቋት የለ? **ይህን ሳስታውስ ግን እጅግ የሚያስለቅሰኝና በአሁኑ ማንነቴ ላይ ሁኜ እንኳ የሚያሳዝነኝ አገሪቱ በሞት ያጣችው ያ! የሰላ አእምሮ ባለቤት የነበረው ልበ ሙሉ ወጣት ትውልድ ነው፡፡ ከእንግዲህ ወዲህ አገሪቱ የፈለገውን ያህል ብርቱ ምጥ ብታምጥ እንኳ ዳግም ልትወልደው የማትችለው ልዩ ትውልድ!!! በጥበቃ ስር አቆይቶና አሳምኖ ጥቅም ላይ ከማዋል ይልቅ በማትረባ ፍየል ቀረርቶና ፉከራ እንደ ቅጠል እንዲረግፍ የተደረገ ብርቱ**

**ትውልድ!!! እጅግ ታላቅ ፀፀትና ፈውስ የሌለው የታሪክ ጠባሳ በየቤቱ በር እያንኳኳ ሳይሆን በጉልበት እየሰበረ የገባበት ሌላው "ጩኸት በራማ" የተሰማበት ብቻ ሳይሆን የታየበት የጨፍጫፊዎች ዘመን ነበር፡፡ የትናንትን ታሪክና፣ በእጁ ላይ ያለውን የራሱን የዛሬ ማንነት በመረጃነት ተጠቅሞ የነገውን ብሩህ ተስፋ አሻግሮ ማየት በሚችል መሪ ባለመታደላችን አንድ ልዩ ለአገር የሚበጅ በቂ ችሎታና አቅም የነበረውን ትኩስ ኃይል ላይመለስና ላናገኘው አፈር ጫንበት፡፡ ወላድ እናትም ለፍታ ያሳደገችውን ሟች ልጇን ስትወልድ ከገጠማት የበለጠ ምጥ ደረሰባት፡፡ መቼ የወላድ እናቶች ብቻ ሆነና ምጡ! ወንዱ ሁሉ ሳይቀር የማይወለድ ልዩ ምጥ አምጦ የለ?** ይቅርታ! ከርዕሴ በመውጣት **ጭልጥ ብዬ ቀይና ነጭ ሽብር** ውስጥ ገባሁባችሁ፡፡ወድጄ አይደለም እውነተኛ ሃዘን ተሰምቶኝና ያ! ጀግና ትውልድ ከፉኛ ትዝ ብሎኝ ነው!!! ደግሞስ ለእውነት የሚሞት የጀግና ትውስታ ከህሊና ውስጥ መቼ ይጠፋና!!!

ወደ ርዕሴ ልመለስና በተመደብኩበት የሥራ ቦታ ላይ ሁለቱንም ዓይነት (የደርጅቴንና የተቀጠርኩበትን) ሥራዎቼን በማከናወን አንድ ዓመት ከቆየሁ በኋላ ከሦስት አስተማሪዎች ጋር በጥርጣሬ ተይዘን ታሰርን፡፡ በአራተኛ ቀናችን አሁን ካናዳ ከሚኖር አስተማሪ ጓደኛዬ ጋር ከእስር ቤት ለማምለጥ ስንሞክር ጠባቂ ወታደሮች ተኩስ ከፈቱብን፤ ሆኖም ግን አንዳችንም ሳንጎዳ አምልጠን በተለያዬ አቅጣጫ ለየብቻ በረሃ ገባን፡፡ ከዚያም መዝሙራችን በተቃኘ ክራር፡-

**"ፋኖ! ፋኖ!!**

**ፋኖ ደስ ይለኛል፣ ሲታጠቅ ማለዳ፤**
**የሚያበላ መስሎ፣ የሚሸኝ እንግዳ፡፡** (የሚበላው የሌለው "ኢሕአሠ" የሚያበላ በማለት በክራር ሲፋንን አይገርምም!!!)

**የወንድ ልጅ እናት ታጠቂ በገመድ፤**
**ልጅሽን አሞራ እንጂ አይቀብረውም ዘመድ፡፡** ሆኖ አረፈው፡፡ (በእውነትም እናት ልጇን ያልቀበረችበት የ "ትንቢት" ፍጻሜ)

ከስድስት ወር የበርሃ ኑሮ በኋላ ግን ባለሁበት ቦታ ድርጅታዊ ትዕዛዝ ከበላይ አካል ደረሰኝ፡፡ እንዲህ የሚል፡- በከተማ ባለው የማጋለጥ ሒደቱ ላይ የአንተ ስም በብዛት ስላልተጠቀመ እጅህን ሰጥተህ ወደ ከተማ ብትገባ በበርሃ ውስጥ ከምታበረክተው የበለጠ ሥራ መሥራት ትችላለህና ምሕረት ጠይቀህ ከተማ ግባ የሚል፡፡ መታዘዝ አንዱ የታማኝነት መገለጫ ባሕሪ በመሆኑ የት? መቼ? እና ለማን?ለሚሉት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ በመስጠት ለአንድ ለስላሳ ባሕሪ ላለው የወረዳ ካድሬ እጄን ሰጥቼ የንቃት ትምህርት አስጀመረኝ (በእኔ ግምት ያልነቃ አንቂ)፡፡ ካድሬው የሚሰጠኝን ትምህርት በመከታተል ላይ እንዳለሁ የአውራጃው ዞን የኢሕአፓ ሃላፊ የነበረ ሰው ፕሮፌሽናል ሆኖ ሲሰራ ከነበረበት ገጠር መንደር ውስጥ ተይዞ መጣ፡፡ እኔንም በወረዳ ሃላፊነቴ (DC) በመጠኑ ያውቀኝ ስለነበረ ከጠላት ጎን እራሱን በማሰለፍ ለሚሠራው **"አብዮቱን የመካስ"** ሥራ በማለት ያልሠራሁትን ሁሉ ጨማምሮ ከመረብኝ፡፡ አሰልጣኜና መሰል ባልደረቦቹም እጄን ስሰጥ ያልተናገርኩት የተለዬ መረጃ ስላገኙ በእኔ ላይ እጅግ ተናደው ጥርጣሬያቸውን ጨመሩብኝ ፡፡ በዚህ ምክንያትም ለክፍለ ሃገሩ ወህኒ ቤት አሳልፈው ሰጡኝ፡፡

ወደ መታረድ የሚነዳ ወጣት መፈክርና የሞት ጣር ጮኸት (ሁለቱም መልማዮቼ በዚህ ወቅት ነበር **"አሁንም ሕዝባዊ መንግሥት" እያሉ በመጮህ** የተሙቱት/የተገደሉት) በተቀላቀሉበት ስፍራ ለአንድ (ለ1) ዓመት ያህል ከታሰርኩ በኋላ ተፈታሁ፡፡ የተፈታሁበትም ጊዜ ያቋረጥኩትን ትምህርቴን ሊያስጀምረኝ ስላልቻለ ለጊዜው ወደነበርኩበት ሥራ መመለስን መረጥኩ፡፡ ከእስር ወዳመለጥኩበት ወረዳ በመመለስ ለተወሰነ ጊዜ እንደቆየሁ ደግሞ ሌላ ያልተጠበቀ ከፍተኛ መጋለጥ መጣብኝ፡፡ በእኔ ስር የነበሩ፤ ነገር ግን ያላጋለጥኳቸው ልጆች እጅ ከፍንጅ ተይዘው ሲመረመሩ ሁሉን ነገር በእኔና ሳይጋለጥ በቆየው ጠንካራ ጓደኛዬ (አሁን አሜሪካ አገር በሚኖረው)ትከሻ ላይ ሁሉን ነገር ጣሉት፡፡ በተለይ አንድ ዋሻ ውስጥ የተገኘውን ሰፊና ውስብስብ ያለውን የ DC መዋቅር የሚተረጉምላቸው ሰው ባለማግኘታቸውና ሁለታችንም ተስማምተን ጠንካራ አቋም በመውሰዳችን ምክንያት እኔን 4 ጊዜ ጓደኛዬን ደግሞ 5 ጊዜ ቶርች አስገብተውናል፡፡ በወቅቱ የክፍለ ሐገሩ ዋና አስተዳዳሪና የደርግ አባል ከነበሩት ባለስልጣን ፊትም ቀርበን ብዙ የማባባያና የማስፈራሪያ ሙከራ ተደርጎብናል፡፡ **እኛ ግን በወቅቱ ወይ ፍንክች? ያ! ብርታትና ጥንካሬ ታዲያ ዛሬ የት ደረሰ? ያውም ለሞት ሳይሆን ለሕይወት!** ይቅርታ! እራሴኑ ነው የጠየኩት፡፡

የማረሳው ነገር ቢኖር ይህ ጓደኛዬ በምርመራ ጊዜ የእኔ ለ2ኛ ጊዜ መታሰር ቆጭቶት ሁሉን ነገር እሱ ብቻውን እንዳደረገውና እኔ እንደሌለሁበት አድርጎ ለመርማሪዎቹ ይናገር ነበረ፡፡ አልተሳካለትም እንጂ በሆነው ነገር ሁሉ ሃላፊነቱን ወስዶ እኔን ለማስፈታት ያልሞከረው ሙከራ አልነበረም፤ አቤት ጥንካሬውና ታማኝነቱ?፤ ነገር ግን ቤተ ሰቦቼ ይህን ጓደኛዬን ያጋለጥኩት እኔ መስያቸው የበቀል እርምጃ ለመውሰድ ሲዝቱ እንደነበረ ሰምተን ብናዝንም ካለማወቅ የተፈጠረ ስሜት መሆኑን ስንገነዘብ ሃዘናችንን መልሰን ረስተነዋል፡፡ በእርግጥ እዚህ ላይ ቆም ብለው ቢያስተውሉ ኖሮ በእኔ በመጀመሪያው እስራቴ ላይ እሱንና ሌሎችን አለማጋለጤና እስከዚያች ቀን ድረስ ሳይታሰር በሰላም የመቆየቱ ሚስጢር ሊገባቸው በተገባ ነበር፡፡ አንዳንድ ጊዜ ማንነታችሁን በተግባር ፈትኖ

ከሚያውቃችሁ ሰው የበለጠ በሩቅ ያለና ፈጽሞ የማያውቃችሁ ሰው ***“እንዲህ ነው አሉ”*** ወይም ***“እንደዚያ ነው አሉ”*** በማለት ጥላሸት ሲቀባችሁ ይታያል፡፡ **እጅግ የሚገርመኝና የሚያሳዝነኝ ደግሞ ይህ ዓይነቱ ባህሪ “ክርስቲያን” ነኝ በሚለው ሕብረተሰብ መካከል አሁንም መኖሩና መለመዱ ነው፡፡** ወገኖች እባካችሁ ሰውን ቀርባችሁ ወይም በመንፈስ ቅዱስ በኩል ደህና አድርጋችሁ ሳታውቁት “አሉ” በሚል የሰነፎች መረጃ ሰውን አትወቁ! ደግሞም አታውሩ፡፡አሉባልታ ኃጢአት መሆኑንም አንዘንጋ!

በኢሕአፓ አዲስ እንቅስቃሴ ምክንያት ከአንድ አካባቢ የተያዝን ሰዎችን በሙሉ መርምረው ከጨረሱ በኋላ ግማሾችን በጨለማ ቤት ውስጥ፣ ሌሎቻችንን ደግሞ ከጨለማ ውጭ በማሰር በወህኒ ቤቱ ለተወሰነ ጊዜ አቆዩን፡፡ ከዚያም በሚስጢር የወሰኑትን ውሳኔ ተግባራዊ የሚያደርጉበት እለት ከመድረሱ አንድ ቀን ቀደም ብሎ በነበረው ሌሊት እስከ አሁን ድረስ ከሕሊናዬ የማይጠፋ <u>**ሕልም አየሁ፡፡**</u> ***“ሙሉ ሰውነቴ ወደ ገደሉ ውስጥ ገብቶ በሁለቱ መዳፎቼ የገደሉን ጫፍ በመያዝ ተንጠልጥያለሁ፡፡ የገደሉ መድረሻና መጨረሻም ፈጽሞ አይታይም ነበር፡፡ መዳፎቼ ሙጪጭ አድርገው ከያዙት ጫፍ ጀምሮ ወደ ፊት ያለው ስፍራ ደግሞ በለምለም ሳር የተሞላ ሜዳ ነበር፡፡ ከብዙ ጭንቀትና የመቧጠጥ ድካም በኋላ ሰውነቴ ከገደሉ በመውጣት ወደ ሜዳው ተንከባልዬ ወጣሁ፡፡”*** ከዚያም ነቃሁ፤በነጋታው ማታ **ለ17ቱ  ልጆች የሞት ቅጣት** ለቀረነው ደግሞ **የሁለት ዓመት እስራት ተፈረደብን፡፡** እስከ አሁን ድረስ የሚገርመኝ ነገር ቢኖር በእውነት መሞት የሚገባኝ እኔ ሆኜ ሳለሁ ከእኔ ስር የነበሩ ልጆች መሞታቸው ነው፡፡ ***ለምን እንዳልሞትኩ ከሕልሙ ፍቺ ጋር ትርጉሙ የገባኝ በነፍሴ ባለቤት ከተገኘሁ በኋላ ነው፡፡ እንደሚገባ ባልኖርለትም!!!!***

ከሁለት ዓመት በኋላ በ1973 ዓ/ም አጋማሺ ላይ ተፈተቼ ትንሽ ሥራ ከሰራሁ በኋላ መስከረም ወር 1974 ዓ/ም ወደ ትምህርት ቤት ተመልሼ የ12ኛ ክፍል ትምህርቴን በማጠናቀቅ የማትሪክ ፈተና ወሰድኩ፡፡ የማትሪክ ውጤትም ስለመጣልኝ ከ1975 – 1978 ዓ/ም ድረስ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በመቆየት በኢኮኖሚክስ ቢኤ ዲግሪዬን በማግኘት ወደ ሥራ ዓለም ተቀላቀልኩ፡፡ በእነዚህ የትምህርት ዓመታት ውስጥም መተከል በመዝመት **“የዜግነት ግዳጄን”** መወጣቴን አስታውሳለሁ፡፡ የሚገርመው ግን ለተፈናቀሉ አርሶ አደሮች ቤት ልንሠራላቸው ተልከን ሳለ መልሰን ሠራን ባልነው ቤት ግድግዳ ላይ **“አትደገፉኝ!”** ብለን እንለጥፍበት ነበር፡፡ **“የቤቱን ጥንካሬ” በምፀት ለመግለጥ!፡፡** አዬ የወጣትነት ዘመን! የማሾፍና በሕይወት ላይ የመቀለድ ወቀት፡፡

በዚህ ሁሉ የሕይወት ውጣ ውረድ ውስጥ ባልፍም ግን ያች ሳትበዛ በትንሿ የተቀነጨበች **“የዲያሌክቲካል ማተሪያሊዝም”** ጥናት እግዚአብሔርን ጭራሽ እንዳስካደችኝ ነበርኩ፡፡ እንዲያውም አስታውሳለሁ የድፍረታችን ድፍረት ከመታሰራችን በፊት በፍስለታ ጾም ጠዋት ጠዋት የእንቁላልና በቅቤ ያበደ ፍርፍር እንክት አድርገን በመብላት ከሰዓት በኋላ ከሕዝቡ ጋር ወደ **ቤተ ክርስቲያን በመሄድ እናስቀድስ ነበር፡፡** ይህም በግልጥ ሃይማኖትን በመቃወም ሥጋ ይበሉ የነበሩትን **ካድሬዎች ለማስጠላትና ለማስወገዝ** እንዲመቸን በማለት ጭምር ነበር ድርጊቱን የምንፈጽመው፡፡ በተጨማሪም ትምህርቴን ጨርሼ ሥራ በመያዝ አብሬው እኖር ከነበረውና ከማከብረው የሦስት ጊዜ ታላቅ ወንድሜ ቤት ውስጥ ስኖር እርሱ ጠዋት ማታ ቤተ ክርስቲያን በማዘወተር ሲጾምና ሲጸልይ እኔ ግን ዐርብ እና እረቡዕ ሳልል ለብቻዬ ልዩ ድስት ተዘጋጅቶልኝ በቅባት የራስ ምግብ በትዕዛዝ ይሠራልኝ ነበር፡፡

ሰፈሬ እሪ-በከንቱ (በፒያሳና በአራት ኪሎ መካከል)ስለነበረ ተመርቄ የመንግሥት ስራ ከጀመርኩበት ቀን ጀምሬ  ከማታ እስከ ሌሊቱ 6 እና 7 ሰዓት ድረስ ሁሉን ነገር በማድረግ ማምሸት ብቻ ሳይሆን አድርም ነበር፡፡ ከዚህ የተነሳም እናቴ ለሕክምና አዲስ አበባ መጥታ በነበረበት ጊዜ ሁኔታየን ዐይታ “ልጄ እባክህ በሰከረ ሰው ተገድለህ መርዶ ከመስማቴ በፊት መጠጡንና ሲጋራውን አቁም” በማለት እያነባች መምከሯ ትዝ ይለኛል፡፡ እንዲያውም ልጄ! ባጠባሁ ጡቴ ይዤሃለሁና እባክህ ተው በማለት መለመኗን አስታውሳለሁ፡፡

ወዮ ጉድ! እናቴ አላወቀችም እንጂ መች መጠጥና ሲጋራ ብቻ ሆነና የዚህ ከንቱ ልጇ ጠላት፤ ፍየል ይመስል ሁልጊዜ ቅጠል ማኘኩ፣ በቁማር ጨዋታ ገንዘብ ማባከኑ፣ ከቤት ወጥቶ ማደሩ(ጎን ማሳረፊያ በተገኘበት ሁሉ /ቱቦም ሊሆን ይችላል/) የት ቀረና? ደግሞስ ማን ምክር ሰምቶ ሊመለስላት? ይህን ዓይነቱን ከንቱ የስካር ሕይወት ነው እንግዲህ ለ5 ዓመት (ከ1979 – 1983 የካቲት ወር ድረስ) የኖርኩት! ፤ የመኖር ትርጉሙ ይህ  ከሆነ! እጅግ የሚያሳዛነው ደግሞ ከእናቴ በስተቀር አንድም ሰው (ተቆርቋሪ የቅርብ ዘመድ ወይም ጓደኛ) ቀርቦ ተው በማለት የመከረኝ ወይም የተቆጣኝ አልነበረም፡፡ እንዲያውም ጋብዘኝ ወይም ልጋብዝህ የሚል ጥያቄ በማቅረብ ከማነሳሳትና ከማበረታታት በስተቀር፡፡ ተያይዞ ገደል ይሏል ይህ አይደል!፡፡

ጊዜው 1983 ዓ/ም አጋማሽ ላይ ነው፡፡ ለመማሬ ምክንያት የሆነውን ወንድሜን፣ ከዚያም ፍቅርና ጀግንነት ያስተማረኝን አባቴን በሞት ያጣሁበትና በሁሉ ነገር ተስፋዬ ሙጥጥ ብሎ ያለቀበት ክፉ ወቅት!!! በነበረኝ እግዚአብሔር የለም አቋሜ ምክንያት ባላምንበትም የወንደሜን ተስካር ሰንጋ ጥዬና የደረቆት ጠላ አስጠምቄ በ40ው ዕለት እሪ በከንቱ ቤታችን ውስጥ አወጣሁለት (የሚጠቅመው ይመስል አወጣሁለት ማለቴ አይገርምም) ፡፡ ይህ የደረቆት ጠላ የመጠጥ ጓደኞቼን 4 ኪሎንና ፒያሳን ለሳምንት ያሕል አሰረስቷቸው እንደነበረ ትዝ ይለኛል፡፡ ምን እነሱን ብቻ! እኔንም ጭምር እንጂ!፡፡ የደለበ ሱስን ሃዘን ባያስወግደውም!!!

ሃውልቱንም በተቀበረበት በባታ ቤተ ክርስቲያን (4 ኪሎ ስላሴ አጠገብ ባለው ቤ/ክ) ውስጥ በእብነ በረድ አሰርቼና በዚያን ጊዜ ለማን እንደሚጻፍ ባይገባኝም **"መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ ሩጫውን ጨርሻለሁ ሃይማኖቴን ጠብቄአለሁ....** (2 ጢሞቲዎስ 4፡ 7-8) የሚለውን ቃል በላው ላይ አስጽፌ አስመረኩለት፡፡ ድንገት እውነት ሆኖ ጽድቅ ቢኖር በዚህ መንገድ ባለውለታዬ የነበረውን ወንድሜን ለማጸደቅ ነበር ይኸ ሁሉ ልፋትና ገንዘብ ክስከሳ፤ የሚገርመው ግን ይህን በማድረጌ በወቅቱ የተሰማኝ ሃዘን ቀንሶልኛል እስከ አሁን ድረስም እንኳ ምንም ዓይነት ጥቅም እንደሌለው ብገነዘብም ይህን በማድረጌ ደስታ እንጂ ጸጸት ተሰምቶኝ አላውቅም!

ከወንድሜ ሞት ጋር ተያይዞ በሕይወቴ ላይ በርካታ አሳዛኝና አስደሳች ነገሮች ገጥመውኛል፡፡ ከአሳዘኑኝና ጠባሳው እስከ አሁን ድረስ አልጠፋ ብለው ካስቸገሩኝ ነገሮች መካከል አንዱ ከሚቴ ጋር አብረን እንኖርበት በነበረው ቤት ውስጥ ልጁ ነው ተብሎ በእናቱ በኩል በመጣው በግምት የ12 ዓመት ልጅ ምክንያት በእናቱ እና ጉዳዩ ባልገባቸው በራሴ ቤተ ሰቦች በኩል የደረሰብኝ ንትርክና ጭፍን ጥላቻ ነበር፡፡ እጅግ የሚያሳዝነው ደግሞ እነዚህ የጎዱኝ ሰዎች እስከ አሁን ድረስ ጥፋታቸውን ተገንዝበው ንስሃ እንኳን አለመግባታቸው ነው፡፡(የንስሃ ትርጉም በትክክለ የገባቸው ካሉ ማለቴ ነው) ቢያደርጉት ኖሮ እኔንም እንደ ቃሉ ይቅርታን ይጠይቁኝ ነበረ፤ ነገር ግን አልሆነም፡፡ ሞቴን በሞቱ ጠርቆ ሕይወትን በማብዛት ከዚህ ሁሉ ጉድ ያስጣለኝ ጌታ ፍጹም እንዲረዳቸው ጸሎቴ ነው፡፡

ይህች ሴት ልቅሶ ለመድረስ ብላ እስከነልጁ ቤት ድረስ በመምጣት ለበርካታ ወራት ተቀመጠች፡፡ እኔና አሁን ካናዳ የሚኖረው ወንደሜ በመመካከር ይህ ልጅ እውነተኛ ልጁ ቢሆንም ባይሆንም በወንድማችን ስም እየተጠራ ማደጉን ስለፈለግን ኃላፊነቱን ተቀብለን ለማሳደግ ወሰን፡፡ እናቱ ደግሞ ውርስ እንድታገኝ በማሰብ ቤተሰብም ቢሆን በሀሰት መስክረን ሕጋዊ ማድረግ ብንችል ለእርሷ ብቻ ሳይሆን ለልጁ ጭምር ይጠቅማል ብለን በማሰብ ሁላችንም ተስማምተን ቀጠልንበት፡፡ እኔም ኃላፊነቱን በቅንነት ወስጄ ጉዳዩን እየተከታተልኩ ሳለ "ሕጋዊ ባሌ ጋር በመሆን በምኖርበት ቤት ለወንድሙ ልቅሶ መጥቶ አልወጣልኝ አለ" ብላ በቀበሌ ከሰሰችኝ፡፡ እኔም ነገሩ ገርሞኝ ጉዳዩን በሰማሁበት ማታ ምን እየሠራሽ ነው ለምንስ ይህን ልታደርጊ ቻልሽ በማለት በእርጋታ ስጠይቃት ሕጋዊ ሚስትነቴ ይረጋገጥልኝ ብዬ ነው የሚል የድፍረት መልስ መለሰችልኝ፡፡ እኔም ያልሆንሺውን ለልጁ ብለን በሃሰት ልንረዳሽ እንመስክርልሽ ባልን ምን የተለዩ ነገር ሆኖ ነው ይህን ያሰብሺው? በማለት ደግሜ ብጠይቃትም መልስ ስላለሰጠችኝ፤ እንግዲያውስ የእኔን እንጀራ እየበላሽ ሳይሆን በውጭ ሆነሽ ክሰሽኝ በማለት ቤቱን በነጋታው እንደትለቅ ነገርኳት፡፡

እሷም ምኗ ሞኝ ነው? ልጁን ይዛ በመውጣት ይኸው እኔንም ልጁንም ድርሽ እንዳንል አድርጎ ጠራርጎ አስወጣን በማለት በየዘመዱ ቤት እንባዋን በማፍሰስና ደህና አድርጋ በማሳመን ፍጹም አስጠላችኝ፡፡ ዘመዶቼም እውነት መስሏቸው ስለተባበሩብኝ ሁሉን ነገር ትቼ አብሮኝ ይኖር ከነበረና ጉዳዩን ከሚያውቀው ወንድሜ ጋር ከቤቱ ወጥተን በጅምር ላይ ባለ ቤቴ ውስጥ ገባን፡፡

በእውነት ከልቤ ለመናገር እንደዚህ ያለ አሳዛኝ ነገር በሕይወቴ ገጥሞኝ አላውቅም! እንዲያውም ይህ ጉዳይ ትዝ ሲለኝ እስከ አሁን ድረስ በእውነት ልቤ ያለቅሳል!፤ ምክንያቱም ምንም እንኳን በዚያን ጊዜ ጌታን ባላውቅም መልካም የሆነውንና ለልጁ በስርዓት ማደግ ስል በፍጹም ቅንነት ሁሉን ነገር አደርገው ስለነበረ ነው፡፡ አስታውሳለሁ በዚህ ጊዜ ነበር የካድኩትን እግዚአብሔርን ሳላውቅ በድንገት በመጥራት በእውነት አለህ? መኖርስ የለኽም! ካለህ ለምን ስለ እውነት አትፈርድም እያልኩ ከማላውቀው አምላክ ጋር ሙጉት የገጠምኩት፡፡ የሚገርመውና ደስ ያለኝ ጉዳይ ግን በዚያ አሳዛኝ በነበረ የልብ ስብራቴ ምክንያት ከንጉሡ ጋር ያደረኩት ሙግቴ ለመልካም ሆኖልኝ በፍቅሩ መገኘቴ ነው! አ! ልብን እንጂ ፊትን ብቻ ዐይቶ የማይፈርድ አምላክ ባይኖር ኖሮ ምን ይሆን ነበር? የቅርብ የምንላቸው ሁሉ ባይረዱኝና ጠልተው ለዩ ስም ሰጥተው ለሰው ሁሉ ቢያሳጡንም(ሳ - ትጥበቅ) ልብን በመመርመር ለአዘኑት መጽናናትን ለሚሰጥና ለሚያሳርፍ ጌታ ክብር ይሁንለት! በጊዜው ደርሶ አሳረፈኝ፡፡

## *2) <u>ድህረ ክርስትና ሕይወት፡</u>*

እስከ 1983 የካቲት ወር ድረስ የሕይወት ትርጉም ለእኔ ጠጥቶ መስከር፣ በሲጋራ ጭስ ሳንባን ማቃጠል፣ በእህል ሳይሆን በቅጠል ጉንጪን አሳብጦ ሲያኝኩ መዋልና በቁማር የወር ደሞዝን በአንድ ቀን አስወስዶ በብድር መኖር ሆነብኝ፡፡ በሌላ አባባል አራት ዓመት ሙሉ በሕዝብ ገንዘብ ዩኒቨርስቲ ገብቶ የመማር ውጤቱ ሕይወቴን ለማጥፋት የሚያስችል ገንዘብ/ደሞዝ ማግኘት ብቻ ሆነ፡፡ በገዛ እጅ መራራ ጽዋ መጨለጥና በጠራራ ፀሐይ ሰክሮ የመቅበዝበዝ ሕይወት!፡፡ በዚህ ማንነቴ ላይ ደግሞ አይደለም ማድረግ ይቅርና ጭራሽ ባለሰብኩት ጉዳይ ላይ አንዳንድ የቅርብ ዘመዶቼ በጭፍን ሰለዘመቱብኝ እጅግ አዝኜ የደም እንባ አነባሁ፡፡

እንግዲህ ሕይወቴ በዚህ መልኩ ምስቅልቅል ባለበትና እጅግ የምወደውንና የማከብረውን ወንድሜን በሞት ባጣሁበት በ1983 ዓ/ም መጋቢት ወር ላይ (ኢሕአዴግ አዲስ አበባን ሊይዝ ሦስት ወር ሲቀረው) ነበር አንድ ያላሰብኩት ጥያቄ ወደ አእምሮዬ ውስጥ በመግባት የተሰነቀረብኝ፡፡ ጥያቄውም ለእኔ መልካምና እንዲህ የሚል ነበር፡-

**""ክርስትና" የሚለው ስም ማንም ሰው እንደሚገነዘበው ክርስቶስ ከሚለው የተገኘ ነው፡፡ ለምድነው ታዲያ ምንጩና መሰረቱ ይህ አንዱ ክርስቶስ ከሆነ፡- ኦርቶዶክስ፣ ካቶሊክ፣ ጀሆባና ፕሮቴስታንት/ጴንጤቆስጤ የሚለው የተለያዬ ስምና ልዩነት የመጣው?" የሚል ጥያቄ፡፡**

ይህን ሳላስበው ወደ አእምሮዬ የመጣውን ድንገተኛ ጥያቄ በወቅቱ ማንም ሊመልስልኝ አልቻለም፡፡ የእኔ ውሳኔ በአንፃሩ ግን ለዚህ ጥያቄዬ ተገቢና አሳማኝ የሆነ መልስ ለማግኘት <u>በሪሰርች የተደገፈ ጥናት ማድረግ የሚል ውሳኔ ነበረ</u>፡፡ (ውጤቱ አልሰሜን ግባ በሉት ሊሆን) ከዚያም በውሳኔዬ በመጽናት(ማን እንዳፀናኝ አሁን ነው የገባኝ) ጥናቴን በተናጥል እንደሚከተለው አካሄድኩ፡-

### 2.1) በኦርቶዶክስ ቤ/ክርስቲያን አጠቃላይ ታሪክ ላይ ጥናት፡-

ከአመሰራረቷ ጀምሮ አምልኮዋ፣ ቅዳሴዋ፣ የትምህርት አሰጣጥና ይዘቱ፣ለክርስቶስ ኢየሱስ ያላት ስፍራ፣ ለቅዱሳን መላዕክትና ለጻድቃን ሰዎች የምትሰጠው ስፍራ እና የተከታይዋ ሕዝብ እውቀት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ምን እንደሚመስል በማጥናትና በማገባደድ ላይ እንዳለሁ ሳላውቀው በድንገት **"የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ቅናት"** ይዞኝ እራሴን አገኘሁት፡፡ ይህም በአራት ኪሎ ስላሴ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሰንበት ትምህርት በመከታተል ላይ እንዳለሁ ያገር ፍቅር ሰሜቴ ተቀስቅሶ ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውለታ ጋር(ለአገር) ስለተቀላቀለብኝ ሌሎችን አምርሬ መጥላት ጀመርኩ፡፡

አስታውሳለሁ ጴንጤዎች አናግረውኝ ይቅርና ድንገት በአጠገቤ ማለፋቸውን ከተረዳሁ እረክሻለሁ በሚል ስሜት እንደ አራስ ሴት ጸበል እረጭ ነበር፡፡ እንዲያውም እኛ የራሳችንን ሃይማኖት (የእኛና የእነሱ የሚል ክርስትና ያለ ይመስል) እንደሚገባ ባለማወቃችን ነው የተበለጥነው፤ ስለዚህ ማንነታችንን አውቀን ልካቸውን ማሳወቅ አለብን በሚል መፈክር በሃይል መንቀሳቀስ መጀመሬ ትዝ ይለኛል፡፡

ነገር ግን በዚህ ሁኔታ እያለሁ ቅናቴና ፉከራዬ ድንገት ባላወኩት መንገድ እየቀዘቀዘ ሄደ፡፡ በምከታተለው የሰንበት ትምህርት ላይ የሚያስተምሩት ሰዎች የማስተማር ብቃትም ከግምቴ በታች ሆኑብኝ፡፡ እንዲያውም ሁልጊዜ ስለሌሎች (ስለጴንጤዎች) መጥፎነት ብቻ የሚሰብኩ ሰባኪዎች!፤ እኔ ደግሞ ጥሎብኝ ስለሌላ ሰው/ማሕበር ድካም የሚነገር ወሬ ስሰማ ጆሮዬን ያምኛል፡፡ እንዲያውም እንደዚህ ዓይነቱ ነገር የተወራበትን ሰው/አካል ማንነት ጠንቅቄ ለማወቅ የበለጠ ያነሳሳኛል፡፡ ከዚህ የተነሳም ጴንጤዎችን ጠጋ ብዬ ለማጥናት ወሰንኩ፤ ከዚያ በፊት ግን ካቶሊክን ማጥናት ወሰንኩ፡፡

### 2.2) በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ላይ ጥናት፡-

በአዲስ አበባ ካቴድራል ትምህርት ቤት ውስጥ/አጠገብ ካለው ቤተ ክርስቲያን ለተወሰነ ጊዜ መመላለስ ጀመርኩ፡፡ ወደ ቤተ ክርስቲየኑ አዳራሽ ውስጥ ዘልቆ የሚገባ ሰው ሁሉ ከመግቢያ በሩ አጠገብ በውስጥ በኩል በሰው ቁመት ልክ በተዘጋጀ ጎድጓዳ ሳህን ላይ ካለ ውኃ ውስጥ ጣቱን ነክሮ በማውጣት አራት አቅጣጫ አማትቦ (መነሻው ምን እንደሆነ ባይገባኝም ከውሃው በስተቀር በጣት ማማተቡ በኦርቶዶክስም አለ) መግባት አለበት፡፡

ይች ቤተ ክርስቲያን ከኦርቶዶክስ ጋር ብዙ ብትመሳሰልም በታቦት ብዛት እንደ ኦርቶዶክስ አትታማም፤ ነገር ግን እኛ ከማን እናንሳለን ውድድር ነው መሰለኝ በመናገሻ ከተማዋ በሮም የሌለ መሆኑ እየታወቀ በኢትዮጵያ እንዲኖር መሞከሩ ያስገርማል፡፡ ምናልባት አገሪቱ ከታቦት ጋር የሆነ ቁርኝት ሳይኖራት አይቀርም ያስብላል፡፡ ሌላው ይችን ቤ/ክርስቲያን ልዩ የሚያደርጋት ነገር ቢኖር ለማርያም ያላት አመለካከት ነው፡፡ እንዲያውም አብዛኛዎቹ የማምለኪያ አጸዶ**ቿን** በኢሳያስ 44፡15-25 ላይ በተጠቀሰችው ሴት ጣኦት ስም "የሰማይ ንግሥት" (our lady- the Queen of heaven) በማለት መሰየማቸው የቱን ያህል ከቃሉ እንደራቀች የሚያመለክት ነው፡፡ ይህ እና ቆቡን ያጠለቀ ጳጳስ የባቲካን አምባሳደር በመሆን በአዲስ አበባ ከተማ መኖሩና ማየቴ ጥናቴን ብዙ እንዳልቀጥልበት አደረጉኝ፡፡ ክርስቲያን በፖለቲካ ሳይሆን በመልካም አስተዳደር መሳተፍ እንዳለበት አጥብቄ ባምንም ከዚህ ዐለም መንግሥት ጋር ግን ጭልጥ ብሎ መደባለቁን ውስጤ አልቀበል አለኝ፡፡

በአጠቃላይ እነዚህ ሁለቱ አንጋፋ የብዙ እድሜ ባለፀጋ ቤተ ክርስቲያኖች የተነሳሁበትን **"ክርስትና- ከክርስቶስ"** የሚለወን ጥያቄዬን በፍጹም ሊመልሱልኝ አልቻሉም፡፡ ምክንያቱም ስብከታቸውና ትምህርታቸው በአብዛኛው የሚያተኩረው በቤታ እናት በማርያም፣ በቅዱሳን ሰዎችና መላእክቶች ላይ እንጂ ክርስትና የሚለው ስም የተገኘበትን ክርስቶስን አልሆነልኝም፡፡ እንዲያውም ይህ ዓይነት ማንነታቸው በተለይ "የአባቴ የእናቴ" በማለት ከአገር ፍቅር ጋር ተቀላቅሎብኝ ቅናት አስይዛኝ የነበረችው ያደኩባት የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ምንም እንኳን መልካም ነገ**ሯ** እስከ አሁን ድረስ ከልቤ ባይጠፋም በሰባኪዎ**ቿ** ድካም ምክንያት ሳላውቀው ራቅ**ኋ**ት፡፡ ከዚያም ወደ ሦስተኛው ጥናቴ አመራሁ፡-

## 2.3) በጆሆቫ ዊትነሶች ላይ ጥናት፡-

አንድ ቀን አራት ኪሎ ታክሲ እየጠበቅሁ ሳለ ሁለት ልጃገረዶች በስእል ያጌጠ መጽሔት ይዘው ተጠጉኝ፡፡ መልከ ቀና የሆነችው መልከ መልካሟ ልጅ ቀልቤን ክፉኛ ሳበችው፡፡ የፈለገችውን እንድትናገር እድል ሰጠኋት፤ እኔ ግን በቁንጅናዋ ተመስጬ እንዴት አድረጌ የራሴ ማድረግ እንዳለብኝ አስብ ነበር እንጂ የምትለውን አልሰማትም ነበር፡፡ ከዚያም ንግግሯን ስትጨርስ እንደገና ለመገናኘት እንድንችል ጠይቁያት ስለፈቀደችልኝ በሚቀጥለው ቀን ለመገናኘት ወስነን ተለያየን፤ "ሁሉ አማረኝን ገበያ አታውጧት" ይሏል ነገር፡፡ የሚገርመው ግን በቀጠሮው እለት ከሌላ ጎረምሳ ጋር በመምጣት ሃሳቤን አመከነቺው፡፡ ከዚያም ይባስ ብላ ወደ ወላጆቿ ቤት በመውሰድና ከእናቷ ጋር በማስተዋወቅ 'Truth' የምትለዋን መጽሐፋቸውን አብረው አስጀመሩኝ፡፡የቃልና የሎጂክ አቀራረብ እውቀታቸው ስቦኝ ለአራት (4) ወራት አብሬያቸው ቆየሁ፡፡ ከዚያ በኋላ ግን "በስላሴ" ትምህረትና በጌታ ኢየሱስ አምላክነት ላይ ተጨቃጭቀን ተለያየን፤ የእኔም ድብቅ ሃሳብ ከሸፈ፡፡የቃሉ እውቀት ሳይኖረኝ ከነዚህ ሰዎች እንዴት ብዬ በቀላሉ እንዳመለጥኩ አሁን ሳስብው ግን እጅግ እገረማለሁ፤ በቀላሉ የሚለቁ ሰዎች ስላልነበሩና ስላልሆኑ፡፡

## 2.3) በፕሮቴስታንት/ጴንጤዎች ላይ ጥናት፡-

አንድ ለአራት (4) አመት ትምሕርት ቤት አብሮኝ የነበረ ልጅ መንገድ ላይ አገኘኝ፡፡ ከዚያም ያውቀኝ የነበረው ማንነቴ በክሳት ምክንያት ተለውጦበት በመደነቅ አዝኖ ጠየቀኝ፡፡ በወንድሜ ሞት ምክንያት እንደሆነ ገቦቶት ሁላችንም ተረኛ መንገደኞች መሆናችንን እያስረዳኝ ምሳ ሊጋብዘኝ ወደ አሰበበት ሆቴል ወሰደኝ፡፡ ምሳ ታዞ ልንበላ ስንል አንገቱን ዘንበል በማድረግ መጸለይ ጀመረ፡፡ ለ4 አመታት ያላወኩትን ማንነቱን ገልጾልኝ እየበላን ስለ ሕይወት ወንድማዊ ምክሩን ከልቡ ለገሰኝ፡፡ ወዲያውም ምን ትጠጣለህ? ሲለኝ ያለምንም ማመንታት ቀዝቃዛ ቢራ አልኩት፡፡ እጅግ የማረከኝ ትችላለህ፤ ነገር ግን በራስህ ፈቃድና ውሳኔ አንድ ቀን ሲገባህ ታቆማለህ፤ የሚለው መልሱና በተከታታይ "መጸሐፍ ቅዱስህን ባለህበት ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሆነህ በማስተዋል አንብብ" በማለት የመከረኝ ምክሩ ነበረ፡፡ በእኔዎቹ የኦርቶዶክስ(ባይገባኝም ሳላውቀው ለካ ኦርቶዶክስ ነበርኩ) ሰባኪዎች የተማርኩት ግን አባብለው ይወስዱችኋልና የሚሉትን አትስሟቸው፤ እንዲያውም አትቅረቧቸው የሚል ስለነበረ ይህ ምክሩ በቤተ ክርስቲያኔ ላይ የነበረኝን ክብርና ግምት ጥርጣሬ ላይ ጣለብኝ፡፡

እነዚህ የጓደኛዬ ምክሮችና በወቅቱ የሰጠኝ የቢራ መጨለጥ ነፃነት (በራሱ ሊያስጥለኝ አለመቻሉን አውቆ ወደሚያስችለው እየቃተተ መሆኑ አሁን ነው የገባኝ) ቀልቤን ስበውት ምክሩን የመስማት ኃይሌን ሳላውቅ በድንገት ጨምረውልኝ አፌን ከፈቼ አዳምጠው ጀመር፡፡ ከጥሩ ምሳ በኋላ ሁለት ቀዛቃዛ ቢራዬንና አንድ ሮዝማን ሲጋራዬን ለጊዜው ፈቅዶልኝ ብወስድም ምክሩና የራሴ ደካማ ድርጊቶቼ ተጋጩተውብኝ ራሴን እንደናቅሁት ሲረዳ "አይዞህ! ሁላችን በዚህ ሁኔታ ነው እግዚአብሔር ረድቶን ያረፍነውና ሰላም ያገኘነው" ስለዚህ "ለአንተም የምትገላገልበት አንድ ቀን አለህ" በማለት መጽሐፍ ቅዱስ ጥናቴ ላይ በማተኮር ከአንድ የስላሴ ዲያቆን ከነበረ የሰፈሬ ሰው ጋር አስተዋውቆኝ በሳምንት አንድ ቀን በመገናኘት ጥናቱን ቀጠልኩበት፡፡

የሰውዬው የትምህርት አሰጣጥ በሳቅ በጨዋታ ስለነበረ ሳበኝ፡፡ ደግሞም እንደሌሎቹ አስተማሪዎች ስለሌላ ሃይማኖት ተሳስቶ እንኳ ለአንድ ጊዜ ሲያነሳና ሲያንቋሽሽ ስላልሰማሁት እጅግ ማረከኝ፡፡ አንድ የትምህርት ርዕስ ከአጠናቀቀልን በኋላ ደግሞ ፈተና ስለሚፈትነን ለተነሳሳሁበት የክርስትና ጥናት ምቹ ሁኔታ ፈጠረልኝ፡፡

በተለይ በልቤ ውስጥ ታትሞ እስከ አሁን ድረስ የቀረልኝ በ1ኛ ቆሮንቶስ 3፡11 ላይ ያለውን ቃል የገለጸበት ስልት ነበረ፡፡ ቃሉም እንዲህ የሚለው ነው፡- "ከተመሰረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልምና፣ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡" እስከ አሁን ድረስ የሚገርመኝ ጉዳይ ግን ወደ ጥናቱ ቦታ ስሄድ በሱቅ አጠገብ ካለፍኩ አንድ ሮዝማን ገዝቼ አንድ ጊዜ ስቤ በመበሳጨት በጫማዬ እርግጠውና ሻይ ቤት ፈልጌ አፌን በሎሚ ካጠብኩ በኋላ ነበር ወደ ጥናቱ ቤት የምገባው፡፡ ትግሉ እንዲህ ቀላል አልነበረም፡፡

የደህንነት ትምህረቴን በዚህ መልኩ ደስ በሎኝ በጥሩ የፈተና ውጤት ካጠናቀቅሁ በኋላ የጥምቀት ትምህርት አስተማሪ ወደ ሆነ ሌላ ሰው ከሌሎች ጋር አብረን ተላለፍን፡፡ ይህን የጥምቀት ትምህርት የተቀላቀልነው በሌላ ስፍራ የደህንነት ትምህርት ከጨረሱ ጋር ስለነበረ ሌላ በጣም የምወደውን የትምህርት ቤት ጓደኛዬን አገኘሁት፡፡ ቆይቶ ሊመጣ ያለውን

መሰናከል ሰው በመሆኔ ባልረዳውም ስንገናኝ ሁለታችንም ደስ ተሰኝተን ልዩ መንፈሳዊ ትርጉም ሰጥተነው እንደነበረ አስታውሳለሁ፡፡ “የፍቅር አምላክ ከልብ የምንቀራረበውን በዚህ መልኩ አገናኘን በማለት፡፡”

የጥምቀት ትምህርቱን ልዩ ልዩ ጥያቄዎችን በጋራ እየጠየቅን እንደሚገባ ካጠናቀቅን በኋላ ገብቷችሁ የምትጠመቁ ወስኑ ሲባል ይህ ጓደኛዬ “የእኛን ቤተ ክርስቲያን ስርዐት.... በሚገባ ማወቅ አለብንና እንቆይ በማለት ስለመከረኝ እንድናፈገፍግ ሆነ፡፡ እኔ ግን የጥምቀት አሰጣጣቸውን ስርዐት ተገኝተን እንድንመለከት ጓደኛዬን አሳምንኩት፡፡አስተማሪያችንም ስለፈቀደልን ሁለታችንም ተገኝተን ስርዓቱን ተካታተልን፡፡ በሂደቱ ላይም ውስጤ ሰለተነካ ጓደኛዬ እየተናደደብኝ ከመቀመጫዬ በመነሳት እንዲያጠምቁኝ ጠየኳቸው፡፡ የሚያስገርመው ግን መልሳቸው ላለመጠመቅ የወሰንከው ስላልገባህ ነውና አሁንም እንደሚገባ ጉዳዩን ሳትረዳ መጠመቅ የለብህም የሚል ነበር፡፡ ይህ መልሳቸው ደግሞ ለማነነታቸው በቂ መረጃ ሆነኝ፡፡ ሥራቸው በእኔው ኦርቶዶክሶች እንደ ተባልኩት አባላትን ለራሳቸው ማብዛት ሳይሆን ባለጉዳዩ ሁሉን ነገር በቃሉ ተረድቶ በእውቀት ማድረግ እንዳለበት የሚያስተምሩ መሆናቸውን ተረዳሁ፡፡

ከዚያም ተጨማሪ የጥምቀትና የቃሉ ጥናት እንድንወስድ አስተማሪ ተመድቦልን እኔ ቀኑ ደርሶ እስከምጠመቅ ድረስ በጉጉት ተግቼ ስከታተል ጓደኛዬ ግን ጭራሹን ሳይጀምር ቆይቶ የአባቱ የእናቱ የሚለውን ኦርቶዶክስነት (ክርስትና እንደ ንብረት በውርስ የሚገኝ ይመስል) አክርሮ ቀጠለበት፡፡ በመጨረሻም ለሁለተኛ ጊዜ የጥምቀት ኮርሴን በማጠናቀቅ ያልምንም ማመንታት ደስ ብሎኝ በመጠመቅ ከክርስቶስ አካል ጋር መቀላቀል ሳይሆን ተጣብቄ ቀረሁ! ቀረሁ!! ቀረሁ!!!

መጠጡንና ጫቱን ለማቆም ብዙም አልከበደኝም ነበር፤ ነገር ግን የሲጋራዋ ጉዳይ እስከ ሁለተኛው የጥምቀት ትምህርቴ መጨረሻ ድረስ አብራኝ በመቆየት የደህንነቱንና የጥምቀቱን ኮርስ ደህና አድርጋ ተካታትላለች፡፡ አንድ ቀን ግን ድንገት ልክ ከሰው እንደሚወጣ ፋንድያ ጠንብታኝ ደህና ሰንብች ተባለች፡፡ የሚገርመው ግን ሰክሬ ቶቦ ውስጥ ስንከባለል ለአንድ ቀን እንኳን በአጋጣሚ ተው ይቅርብህ ያላሉኝ ዘመዶቼና ጓደኞቼ ተቆርቁረው ምን ጎሎህ ነው የተበላሸኸው? ማለት አበዙብኝ፡፡ በዘመድ ጉባዔ ፊትና በ11 ማሕበርተኞቼ ፊት ቀርቤ ተመክሬያለሁ፡፡ ይህ ድርጊታቸው ግን ለእኔ እጅግ እንዳስተውልና የበለጠ እንድቀጥልበት ረዳኝ፡፡ ብርሃኑን ጨለማ፣ ጨለማውን ብርሃን የሚሉ መካሪዎች መሆናቸው ነው፡፡

ይህ በእንዲሕ ሁኔታ ቀጥሎ እያለ ክፍለ ሀገር ለምትኖረው እናቴ ሰዎች በቀጥታ በመሄድ “ልጅሽ ሰለመ” ብለው ሲነግሯት ልጄ አያደርገውም በማለት ወደ አዲስ አበባ በፍጥነት መጣች፡፡ ስታይ ልጇ ያ! በመጠጥ ምክንያት ሰው ይገድለዋል ብላ ተስፋ ቆርጣ የተወችው ሳይሆን በጊዜ ገብቶ በመበርከክ ጌታ ሆይ እያለ የሚጮህና እናቱን እንደ ቃሉ የሚንከባከብ ሌላ አዲስ ልጅ!!! ከዚህ ሁኔታ ተገርማ በመነሳት ነበር “ልጄ ምን ብለው ነው ሰለምክ” ያሉህ? በማለት ተገርማ የጠየቀችኝ፡፡ እኔም ማንነቴን አይተሽ ለጥያቄው እራስሽ መልስ ስጪ በማለት ጥያቄዋን ወደራሷ መለስኩት፡፡ በመጨረሻም በርታ ከእንግዲህ በሰው እጅ እንደማትሞት አረጋግጫለሁ በማለትና እኔም የጌታን ነገር ነግሬያት ወደነበረችበት በሰላም ተመለሰች፡፡ በመጨረሻም ከተወሰኑ ዓመታት በኋላ የዐመት ፈቃድ ወስጄ ለሁለት ሳምንታት የጌታን ነገረ እያስረዳኋት ቆይቼና ንስሃ ገብታ ጌታን እንደትቀበል አድረጌ ወደ አዲስ አበባ በተመለስኩ በአንድ ወር ውስጥ ሳትታመም በተኛችበት ላትመለስ አሸለበች - ሰዎች ሲያረዱኝ ለእኔ ግን ሰርግ የተጠራሁ ነበር የመሰለኝ፡፡ አቤት የንጉሡ አሠራርና አጠራር!!!

ሌላው የክርስትና ሕይወቴ ተስማምቶኝ እየጣመኝ ባለበት በ1998 ዓ/ም የታቦር ሴራሚክ ተጠባባቂ የንግድ ሥራ አስኪያጅ ሆኜ ስሰራ መንግሥት በጴንጤነቴ አምኖኝ ጀርመን፣ ሆላንድና ቤልጄዬም የሥራ ጉብኝት እንዳደርግ ልኮኝ ሳለ ጀርመን ላይ አንድ የማውቀው ወንድም እጅህን ስጥና ቅር ሲለኝ የመለስኩለት መልስ “መንግሥት አምኖ የላከኝ በክርስትናዬ ምክንያት ስለሆነ ፈጽሞ አላደርገውም፤ ጌታ ሲፈቅድ በፈለገው ወቅት ሊያወጣኝ ወይም በኢትዮጵያ ሊያኖረኝ ይችላል በማለት በእምነት የመለስኩት ትንቢታዊ መልስ በተመለስኩ 5ኛ ዓመቴ ላይ እውን ሆኖ ኑሮዬን በውጭ አገር ጀመርኩ፡፡

የማረሳው ፈተና ግን በአንድ የመንግስት መስሪያ ቤት ውስጥ በተ/የንግድ ሥራ አስኪያጅነቴ ወቅት ሳላውቀው የያዝኩት ቦታ የጉቦ ዋና በር ስለነበረ ሁለት ነጋዴዎች (አንዱ የመርካቶ ጮሌ እስላም የነበረና በዘመቻ ፈልጾስ መስከሬለት በታላቁ ተልእኮ እንዲያዝ የተደረገ፣ ሁለተኛው የደብረ ብርሃን አክራሪ ኦርቶዶክስና ነጋዴ) ባእልን ምክንያት አድርገው በፖስታ የታሸገ በርካታ ገንዘብ ቢሮዬ ድረስ በማምጣት በእንኳን አደረሰህ ሰላምታ በየግላቸው ሊያስረክቡኝ ሞከሩ፡፡ ለእኔም ጌታ ፀጋውን አብዝቶልኝ በቢሮዬ ውሰጥ አንዳንዴ የምጠቀምበትን መጽሐፍ ቅዱስ በማውጣትና በማስረዳት መልሰው እንዲወስዱ ማደረጌን አስታውሳለሁ፡፡ በዚህ መልኩ በሚመጣ ገንዘብ ይጠቀሙ የነበሩ የበላይ አለቆቼ ግን ሳላውቀው ጠሉኝ፡፡ ከዚያም በሥራ አመራር አባልነቴ መካፈል ሲገባኝ አንድ ቀን እኔ ያልተገኘሁበት ስብሰባ በዋና ሥራ አስኪያጁ አዘጋጅነት በድብቅ ተሰብስበው በእኔ ቦታ ላይ ሌላ ሊቀጥሩ ወሰኑ፡፡ እኔም ጉዳዩን በመስማቴና ምክንያቱን በመረዳቴ የመልቀቂያ ደብዳቤ በደስታ ጽፌ ሳስገባ ዋና ሥራ አስኪያጁ በደሰታ ተቀብሎ

መልቀቂያውን ወዲያውኑ ሰጠኝ፡፡ ጠበቃ የሆነኝ ጌታዬም ረድቶኝ በሁለት ሳምንት ውስጥ እጥፍ ደሞዝ አግኝቼ ከአንድ NGO ውስጥ ገባሁ፡፡

በአመቱም ያባረረኝ አለቃዬና በእኔ ቦታ ተቀጥሮ የነበረው ሰው በጉቦ ቅሌት ተከሰው ተባረሩ፡፡ የሚገርመው ግን ዋና ሥራ አስኪያጅ የነበረውና በደብዳቤ ያባረረኝ ሰው አንድ ሻሂ ቤት አግኝቶኝ save the Children (NGO) ውስጥ የማውቀው ሰው እንዳለ ሳያፍር በድፍረት ጠየቀኝ፡፡ ሥራ ለማግኘት በለመደው የጥቅምና የወገን መንገድ እንድረዳው ፈልጎ! እንዳጋጣሚ ሆኖ ግን የጠቀሰልኝ ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ የነበረች ክርስቲያን ሴት ከሁለት ቀን በፊት ለሥራ ቢሮ መጥታ ስለነበረ የሰጠችን ካርዷን ሳሳየው ደነገጠ፡፡ በእኔ ላይ ያደረገው መጥፎ ሥራው ትዝ ብሎት! እኔም ጌታ እረድቶኝ በአድሎ ሳይሆን በተገቢው መልክ እንደሚረዳ ነግሬውና ሕሊናው እየወቀሰው ተለያየን፡፡ “ጠላትህ ቢራብ አብላው” የሚለው የወዳጄ ቃል ትዝ ብሎኝ እራራሁለት!!!

በመጨረሻም ያችን በሃሰት መስክሬ ሕጋዊ የወንድሜ ሚስት ላደርጋትና ልጇንም በቅንነት ተቀብዬ ላሳድግላት የነበረችውን ሴት አንድ ቤ/ክርስቲያን የአምልኮ ፕሮግራም ላይ አገኘኋት፡፡ በሞተ ማንነቴ ውስጥ ስለነበርኩ ደስ ብሎኝ ስስማት አላመነችኝም፡፡ በተሰጠኝ ፍቅር አረጋግቻት እውነቱን ካስረዳኋት በኋላ ግን እንባዋን በማፍሰስ ከልቧ ንስሃ ገብታ አላወኩህም ነበርና ይቅርታ አድርግልኝ ስትለኝ “በዚያች ቅጽበት በሰማይ በመላእክት ዘንድ ካለው ደስታ የተካፈልኩ” እስኪመስለኝ ድረስ በአዲሱ ማንነቴ አቅፌያት አብረን መላቀሳችን ትዝ ይለኛል፡፡ ለሥጋ ለባሽ (ያውም ለእኔ ጉደኛው ማንነቴ) የማይቻለውን ላስቻለኝና ለአስቻላት አዳኝ ጌታ በስፍራው የነበሩ ወገኖች ሁሉ እስከሚገረሙ ድረስ በታላቅ ጩኸት ክብር ሰጥተን ተቀመጥን፡፡ ፕሮግራሙም ሲያልቅ ያለፈውን ፍጹም ረስተን ያገኘነውን ሕይወት እንድናጣጥመውና ልጁንም በፍቅርና በመመካከር እየተረዳዳን እንድናሳድገው ለጊዜው ወስነን በሰላም ተለያየን፡፡ ከዚያ በኋላም አንዳንዴ ቤት ድረስ በመሄድ ሌላ ጊዜ ደግሞ በተለያዬ መንፈሳዊ ፕሮግራም ላይ ልጁን በመያዝ እየተገናኘን መመካከሩን ቀጠልንበት፡፡ ወደ ውጭ አገር ስወጣም ትዳር ለመያዝ ብየ ያዘጋጀሁትን ጠቅላላ የተሟላ የቤት እቃዬን (ቲቪ፣ሶፋና አልጋ ሳይቀር) ልጁ ሰው እንዲሆን በማሰብ በደስታ ሰጠሁት፡፡ በተጨማሪም ካገር በወጣሁ ትንሽ ጊዜ ውስጥ ገንዘብ አጠራቅሜ ንግድ ልጀምር ፈልጌ 10000 ብር ጎደለብኝ ብሎ ስለጠየቀኝ አሁንም ሰው ሆኖ ወንድሜን እንዲተካልኝ ካለኝ ጽኑ ፍላጎቴ የተነሳ ደስ ብሎኝ ሰጠሁት፡፡ ከዚያ በኋላ ግን እሱም ሆነ እናቱ የውኃ ሽታ ሆኑ፡፡ አሁንም ክብር ለጌታዬ ይሆን! እኔም ጭራሽ አልጎደለብኝም!!! ካገኘኋቸውም የተቀየረልኝን ልዩ የፍቅር እጅ ዘርግቼ በማቀፍ እቀበላቸዋለሁ፡፡

የሚገርመው ደግሞ በሁለተኛው እስራቴ ወቅት እጃቸውን የሰጡ ይፈታሉ የሚለውን ዜና የሰማቸውና ምንም ነገር የማታውቀው ልጃገረድ እህቴ የክፍለ ሀገሩን የደርግ ተወካይ ባለስልጣን ቢሮ ድረስ ሄዳ ወንድሜ እጁን ሰጥቶ ስለሆነ የታሰረው በተባለው መንገድ መሰረት ይፈታልኝ ብላ ስትጠይቅ ካወቅሺበት ይቻላል በማለት ለተሰጣት የጥያቄ ጥያቄ መለስ “የወንድሜን ሕይወት ካተረፍኩ ሴት አዳሪ ብሆንስ” ምን ቸገረኝ ማለቷን ሰምቼ በማስጠራት“ዳግመኛ ወደዚህ ሰው ቢሮ ሄደች መባልን ከሰማሁ እራሴን እንደምገልና ደግሞም ከዚህ ሁሉ ወጣት እኔ የተለየሁ ስላልሆንኩ ሁሉ እንደሆነ እሆናለሁ” ብዬ በማስጠንቀቅ ከአውሬ ያመለጠችና ከወንደሞቿ ሁሉ እጅግ አብልጬ እወዳለሁ ትለኝ የነበረቺው እህቴ ጌታ ካገኘኝ ጊዜ ጀምሮ ጦር ትሰብቅብኝ ገባች፡፡ ወዶ አለማስተዋል ሆኖባት! እንዲህ ዛሬ እሷም ሆነች ሌላው “ለራሱ መሆን ያቃተው” ወንድሜ ጭምር በአንድነት በጌታ ፍቅር ተገኝተው በእግሩ ስር ለመውደቅ ላይቀርላቸው!!! ወሰን የሌለው ፍቅሩ አያስደንቅም?

እኔም እንግዲህ በዚህ ሂደት ላይ እንዳለሁ ነው የማዳን ቃሉ ሰይፍ ቀስ እያለ ጅማቴን፣አጥንቴንና ቅልጥሜን ሳያሳምም ወግቶ በመፈወስ ወደ ፍቅሩ መንግሥት ያፈለሰኝ፡፡ አቤት! አሠራሩና አደራረጉ? እግዚአብሔር የለም ይል የነበረውን እውቀት የለሺ ከሃዲና እንዲሁም ጴንጤ ሊደፍረው የማይችል የሚመስለውን ተደባዳቢ ወሮ በላ የሰማይ መልዕክት ሲያገኘው አይገርምም? እሱስ (ጌታዬ!) መችም የጠፋውን በፍቅሩ ፈልጎ ማግኘትና መፈወስ መለኮታዊ ባሕሪው ነው፤ ነገር ግን ሰውን ያህል አስደናቂ ፍጡር አጥፍቶ (በኢሕአፓነቱ) የራሱን ዓላማ ብቻ ተግባራዊ ለማድረግ ያን ያሕል ጊዜያዊና ጠፊ ለሆነ ነገር ዋጋ የከፈለ የዚህ ጽሑፍ ጸሐፊ ይህን የተደረገለትን የማዳን ውለታ በመዘንጋትና ቸል በማለት እንቅልፉን ተኝቶ የሚያድር መሆኑ ነው የሚያስገርመኝ፣ የሚያሳዝነኝና እጅግ የሚያስፈራኝ!!!!!!!!! ኧረ ጎበዝ በጸሎታችሁ እርዱኛና በትንሳኤው ኃይል ተቀጣጥዬ እውነተኛና ትጉህ ሠራተኛ ልሁንለት!!!!!!!!!!!!!!

አቤቱ ጌታ ሆይ! የሚገባውን በትጋት በማድረግ ያከብርህ ዘንድ
እባክህ ደካማ ባሪያህን በመንፈስህ እርዳው??? አሜን፡፡

ፍቅሩ ከአእምሮ በላይ ለሆነው አዳኜ
ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ይሁንለት!!!

***ትንሺ ምክር ቢጤ እነሆ!***
***ይህን ጽሑፍ በትዕግስት***
***አንብባችሁ ለጨረሳችሁ!!!***

***ያላመለጣችሁ ወገኖቼ ሆይ! ልድገመውና ወገኖቼ ሆይ!!!***

ሌባ እንኳ በጥፋቱ ሲያዝ እኔን ያዩህ ተቀጣ ይላል፤ ሊያስተምር!
ታዲያ ከፋንድያ ላይ በፍቅር ጌታ ተነስቶ
ወግ ማዕረግ እያየ ያለ የዚህ ሰው ሕይወት
ጥያቄ ፈጥሮባችሁ በሕይወታችሁ ላይ
ጥናታዊ ምርምር ለማደረግ አያነሳሳችሁምን?
ጀግና ነኝ ይል የነበረ የበርሃው  ወገኛ ፋኖ እንኳ
ያላቅሙና ያለችሎታው ጥናት አደርጋለሁ በሎ
ከሰማይ በመጣ የፍቅር ጀግና
ለውርደት ሳይሆን ለክብር ተሸነፈ (ተጠና)፡፡ ይገርማል! የጌታ አሠራሩ!!!!

በሌላ መጣጥፍ እስምንገናኝ
በቸርነቱ አብረን ቸር እንሰንብት!!!